# በቅንድቡ ውበት ቅናት አድሮባቸው
# እሳት ለኮሱበት እንዲያኮማትረው!

**አዜብ ጌታቸው**

ለዚህ ጽሁፍ በርዕስነት የተጠቀምኩባት ከላይ ያለቺው ሁለት ስንኝ ፤ ከወደ ሸገረ የተቋጠረች ቅኔ ቢጤ ነች። ኢሣት ስርጭት እንደ ጀመረ ከሕዝቡ "እሣት" የሚል መጠሪያ እንደተሰጠው ሳትሰሙ አልቀራችሁም፡፡ እናም በዛው ሰሞን ደግሞ ሰለሞን ተካልኝ በዝቅጠቱ እስካሁን ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ወደር የማይገኝለትን ነጠላ ዜማ ለቆ "የቅንድቡ ማማር" እያለ ሰውየውን ማሞካሸቱ ከኢሣት ስርጭት መጀመር ጋር የተገጣጠመባቸው ወገኖች ነበሩ፡-

በቅንድቡ ውበት ቅናት አድሮባቸው
እሳት ለኮሱበት እንዲያኮማትረው!

ብለው የተቀኙት።ማለፊያ ቅኔ ነች። በነገራችን ላይ ሰሎሞን ተካልኝ ለነጠላ ዜማው ግጥም ሲቋጥር በተለይ የሚደነቅ ውበት ፍለጋ ባዝኖ፤ ባዝኖ፤ ምንም ሊያገኝ ስላልቻለ ቅንድብ ላይ ማረፍ ሳይገደድ የቀረ አይመስለኝም። ሌላ ምን ይበል?

የጽሁፌ ትኩረት በቅንድቡ ውበትና ቅኔ ዘረፋው ላይ አይደለም። የጽሁፌ ጭብጥ የግንቦቱ ምርጫ ውጤት የሚያስከትለውን የአመለካከት ለውጥና የአመለካከት ለውጡም በተቃዋሚው ጎራ የኃይል አሰላለፍ ለውጥ ላይ የሚኖረውን  እንድምታ ለመቃኘት የሚሞክር ነው።ስለዚህ ቅኔውንም ለዘራፊው፤ ቅንድቡንም ላበጣሪው ትቼ ወደ ጉዳዩ ላምራ፡-

የምርጫ 2002 ድራማ በወያኔ ፍጹም የሆነ አሸናፊነት መጋረጃው ከተዘጋ 6 ሳምንታት ተቆጠሩ።ምንም እንኳ የተውኔቱ መቋጫ አንድ ለናቱ የሆነውን ወያኔን አሸናፊ የሚያደርግ እንደሚሆን ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ የታወቀ ቢሆንም፡ ሽፍጡ እንዲህ አይን ያወጣ ይሆናል ብሎ የገመተ ስለመኖሩ ግን እጠራጠራለሁ።(ልደቱ አያሌውን ጨምሮ)

በጥቂቱም ቢሆን ምርጫውን ፍትሃዊ ለማስመሰል  ይሞክራሉ የሚለው ግምት የብዙሃኑ ግምት ነበርና 99.6 % ሕዝብ መረጠን የሚለው ዜና ይፋ ሲሆን፡ ዓለም ጉድ አለ!። የምርጫው ውጤትም ተወገዘ!። ውግዘቱም ሆነ ነቀፌታው ግን ከሚዲያ ፍጆታነት ያለፈ ፋይዳ አልሰጠም። የባለጉዳዩ ሕዝብ ጠንካራ የተቃውሞ ክንድ እንጂ የውጭ ሃይላትና የምርጫ ታዛቢዎች ሪፖርት ምንም ለውጥ ሊያመጡ እንደማይችሉ ወያኔም አውቋል እኛም ከታሪክ ተምረናል።

የሆነው ሆኖ ወያኔም ቢሆን 99.6% በሆነ ውጤት አሸናፋለሁ ብሎ እንዳልገመተ ጠ/ሚሩ አምልጧቸውም ቢሆን ነግረውናል። በርግጥም ከቁጥጥራቸው ውጭ የሆነ ክስተት ተፈጥሮ እንጂ 99.6 % አሸንፍን ማለት ታዓማኒነት እንደማይኖረው ይጠፋቸዋል አልልም።  የሆነውም ይኸው ነው! ።ለያንዳንዱ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ቀለብተኛ አባል በነፍስ ወከፍ በዛ ያለ የምርጫ ካርድ አደሉ፡፡ ሁሉም በታዘዘው መሰረት የተሰጠውን ካርድ ኮሮጆው ውስጥ ከተተ። በየምርጫ ጣቢያው ያለውን መራጭ ሕዝብ ቁጥርና ለአባላት የሰጡትን ካርድ ለማነጻጸር ግዜው አልነበረምና  ወደ ቆጠራ ሲገባ ያልጠበቁት ተከሰተ። በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች  ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያገኘው ድምጽ ለምርጫ ከተመዘገበው ሕዝብ በላይ ሆነ። ይህንኑ አውቀው ታዛቢውን በጠዋት ባያባርሩ ኖሮ ያገኙት ድምጽ  ከ100% በላይ ሆኖ በሳቅን ነበር።

የሚገርመው ደግሞ፡ 99.6 % ሕዝብ የመረጠው ፓርቲ መሪ ደስታቸውን ለመረጣቸው ሕዝብ ለመግለጽ አደባባይ ወጥተው ንግግር ሲያደርጉ፤ ጥይት በማይበሳው መስተዋት መከለላቸው ነው። ማንን ይሆን የፈሩት? 0.04% የሆነውን ሕዝብ? ገሪም ነው...!

የምርጫው ውጤት እንደሚያሳየው ከሆነ፡-የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመድሃኒአለምና ከአላህ ቀጥሎ የሚያምነው በመለስ ዜናዊ መሆኑን ነው።እናም ሕዝቡ እኚህን ቅዱስ መሪ እንኳን በጥይት ሊያጠፋ ይቅርና፤ መለስኤል ተብለው 45ኛ ታቦት ይሁኑ  ቢባል አሁንም 99.6% ያህሉ ሕዝብ አይስማማም ትላላችሁ?። የምርጫው ውጤት የሚነግረን ይህንኑ አይደል። ታዲያ የአቶ መለስ ፍራቻ ለምን ይሆን?

ሌላው ያስገረመኝ ፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያደረጉት እንቅስቃሴ ደካማ መሆኑ ለምርጫው ውጤት አስተዋጾ አድርጓል የሚል ግምግማ ቢጤ ያቀረቡ ጥቂት የማይባሉ ጸሃፍቶችን መመልከቴ ነው። በኔ እይታ ግን፡- የሆነው ሊሆን የቻለው፤ አድራጊና ፈጣሪው ወያኔ! እንዲሆን የፈለገው በመሆኑ ብቻ ነው።አለቀ!። የአንድነት የውስጥ ውዝግብ፤ የመድረክ አብሮ ብዙ አለመስራት፤ ሌላም ሌላም ምክንያቶች ሁሉ ተደምረው ለ99.6% የወያኔ አሸናፊነት 0.0000...1% ያህልም ቢሆን አስተዋጾ አላደረጉም እላለሁ።

ይህን የግምገማ ነጥብ ያነሳሁት አለምክንያት አይደለም። በዚህ የግምገማ ነጥብ ላይ በመንጠላጠልና ለወያኔ አሽናፊነት መገለጫ ምክንያቶቹ መቶ በመቶ የወያኔ አምባ ገነንነት መሆኑን በማደብዘዝ በቀጣይ ምርጫ ተቃዋሚዎች ጠንክረው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል በሚል ዳግም ለምርጫ ተውኔቱ መድረክ ሊዘረጉ የሚሯሯጡ ወገኖችን ለመታዘብ በመቻሌ ነው።ሳታመሓኝ ብላኝ አለች አህዩት!

በግንቦት 7 ምስረታ ዋዜማ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከወያኔ ጋር ሰላማዊ ትግል አያዋጣም። የትግል ስልታችን ሁለገብና አመጽንም ያካተተ መሆን ይገባዋል በሚል አብይ ጭብጥ ዙሪያ አንድ ጽሁፍ ማቅረባቸው ይታወሳል። በዚሁ ጽሁፍ ዙሪያ ከቀረቡላቸው በርካታ ጥያቄዎች መካከል በተለይ ለአንዱ ጥያቄ የሰጡትን መልስ እዚህ ላይ መጥቀሱ ተገቢ ይመስለኛል።

ለአቶ አንዳርጋቸው የቀረበው **ጥያቄ፡-**እርስዎ ከወያኔ ጋር ሰላማዊ ትግል አያዋጣም እያሉ ነው! በተቃራኒው ደግሞ ሰላማዊ ትግሉ መች ተነካና? የሚሉ ወገኖች አሉና ምላሽዎ ምንድነው? የሚል ነበር፡፤

አቶ አንዳርጋቸው ሲመልሱም። የሰላማዊ ትግሉ አልተነካም ሲባል እነ ማርቲን ሉተር ኪንግና ማህተመ ጋንዲ የተጓዙበትን የሰላማዊ ትግል ስልትና ጎዳና እኛም መሞከር አለብን የሚል ዕሳቤ ተይዞ ከሆነ ስህተት ነው።እነ ማርቲን ሉተር ኪንግና ማህተመ ጋንዲ የሰለጠነ ባላንጣ ነበራቸው።ሌላው ቀርቶ ማህተመ ጋንዲ የረሃብ አድማ በሚያደርግበት ወቅት ባላንጦቹ ይሞትብናል ብለው የሚጨነቁ የሰለጠኑ ባላንጦች ነበሩ።ወደኛ ስንመለስ ግን አለመታደል ሆኖ ባላንጣችን ወያኔ የሰለጠነ ባላንጣ አይደለም። ብለው ነበር(ፍሬ ሃሳቡን በራሴ አገላለጽ ነው ያሰቀመጥኩት)

በወቅቱ ይህን የአቶ አንዳርጋቸውን አቋም በተመለከተ ሰፊ ክርክር ሲካሄድ እንደ ነበር አስታውሳለሁ።ይህን አቋም ከሚደግፈው ወገን ባላነሰ ቁጥር የሚቃወም ወገንም ነበር (በሰላማዊ ትግል ተስፋ ቋጥሮ የነበረው)። ዛሬስ? ምስጋና ለ99.6%ቱ የምርጫ ውጤት ይሁንና ዛሬ በነ ማርቲን ሉተርኪንግ የሰላማዊ ትግል ሃዲድ ልሽከርከር፤ የነ ማህተመ ጋንዲን ስልት ልሰልት የሚል ተቃዋሚ ኃይል የሚኖር አይመስለኝም። አለሁ ካለም ራሱን ይመረምር ዘንድ ምክሬ ነው።

ሰላማዊ ትግል ከትጥቅ ትግል በበለጠ አድካሚና ውጣ ውረዱም የበዛ እንደሆነ ይነገራል። በርግጥም ነው።ታዲያ ይህ ዕውነታ መሬት የሚይዘው፡- ድካሙና ውጣ ውረዱ የማታ ማታ ለውጤት የሙብቃቱ ጭላንጭልም ቢሆን ተስፋ እስካለ ድረስ ይመስለኛል። የኛ የሰላማዊ ትግል ታሪክና ልምድ ግን ይህን አመላካች አይደለም። በታገልን ቁጥር የትግል ሜዳው እየጠበበ እንጂ እየሰፋ አልሄደም። በአጠቃላይ በሰላማዊ ትግል የተገኘ አንድም ውጤት የለም ብቻ ሳይሆን የነበረውም ጠፍቷል። ምንም እንኳ ተቃውሟቸው ውጤት ባይኖረውም፤ ትናንት አቶ መለስን ፓርላማ ውስጥ ይሞግቱ የነበሩ የተቃዋሚ ድርጅት አባላት ዛሬ አንድም ወንበር ሊያገኙ አለመቻላቸው ለዚህ እውነታ በቂ ማስረጃ ነው።ያፈጠጠው እውነት ይህ ነው!

ከአሁን በኋላ በተለይ የመድረክ አመራር የሆኑት አቶ ስዬ፤ በተደጋጋሚ ሲገልጹ እንደሚሰሙት፤ ተስፋ ሳንቆርጥ ነገር ግን ወያኔ ከከለለው የሰላማዊ ትግል ሜዳ ሳንወጣ በዚሁ ስልት መቀጠል አለብን የሚል አመለካከት በምንም መመዘኛ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል አይመስለኝም።

የፖለቲካ አመለካከት በምክንያታዊነት ላይ እንጂ በማይጨበጥ ተስፋ ላይ አይመሰረትምና አቶ ስዬም ሆኑ ሌሎች **"ከሰላማዊ ትግል ጋር ፍቅር እስከ መቃብር"** ያሉ ፖለቲከኞች ከማንም በላይ የሚያውቁትን የባላንጣቸውን ባህሪ ገምግመው አመለካከታቸውን ቢያርቁ መልካም ነው እላለሁ።

በተለይ እንደ አቶ ስዬ አይነት የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ነገር ግን ጽኑ የወያኔ ተቃዋሚ ወገኖች፤ ከሰላማዊ ትግል ውጭ ምንም መፍትሄ የለም የሚለው አመለካከታቸው እንደማያዋጣ ወይም ትክክል እንዳልሆነ እያወቁም ቢሆን ጸንተው የሚሟገቱለት፤ በአመጽ ወይም በትጥቅ ትግል የሚመጣ ለውጥ በትግራይ ሕዝብ ላይ አሉታዊ ክስተትን ሊያስከትል ይችላል ከሚል ስጋት እንደሆነ የብዙዎቻችን ግምት ነው።

በመሆኑም ይህን የትግራይ ተወላጆች ስጋት በግልጽ አንስቶና ተወያይቶ፤ በምንም ይሁን በምንም የትግል ስልት በሚመጣ ለውጥ በትግራይ ሕዝብ ላይ ሊደርስ የሚችል ጥቃትም ሆነ በደል እንደማይኖር፤ ሊኖርም እንደማይችል የጋራ ግንዛቤና እምነት ላይ መደረስ መቻል አለበት።

ለዚህ በአንድ ዓላማና ስልት የጋራ ትግል ለማድረግ እንዳይቻል እንቅፋት ለሆነው ችግር መፍትሄ መሻት ግዜው ግድ የሚለው ጉዳይ ነው።

ሌላው ዋና ጉዳይ! የትግል እንቅስቃሴዎች ሁሉ እንደ ከዚህ ቀደሙ ፤ ለግንቦት ምርጫ በመስከረም የሚጀመር ሩጫ አይነት ዕለት አቡኩቶ ዕለት አንጉቶ ሳይሆኑ፡- ረዥምና አርበ ሰፊ ዕቅድን ይዞ የመነሳቱ አስፈላጊነት ነው።

ለምሣሌ፡- በወያኔ ሚዲያዎች ማለቂያ የሌለው ውሸት የደነቆረውና ትክክለኛ ኢንፎርሜሽን የማያገኘውን ሕዝብ ትክክለኛ መረጃ እንዲደርሰው በማድረግ ረገድ እንደ ኢሣት አይነቱን ነጻ ሚዲያ በመደገፍ የሕዝባችንን የመረጃ ትጥቅ ማጠናከር ከምንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው የትግል ምዕራፍ መሆን ይገባዋል።መረጃ ኃይል ነው! ይባላልና ትክክለኛ መረጃ ያለውን ሕዝብ በቀላሉ ማንበርከክ አይቻልም።በዚህ ረገድ ሕዝባችን ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ጥማት እንዳለበት በኢሣት ስርጭት መጀመር ከተሰማው ስሜት መረዳት ከባድ አይሆንም።

ወደ ጽሁፌ መቋጫ ሳመራ፡- የግንቦቱ ምርጫ ውጤት ጥቂትም ቢሆን በሰላማዊ ትግል ተስፋ ቋጥረው ከላይ እታች ሲሉ የነበሩ ወገኖችን ብቻ ሳይሆን፤ ወያኔን ተለማምጠውና ለወያኔ ታዘው፤ በሰላማዊ ትግል ሥም፤ ሰላማዊ ተቃዋሚ ተሰኝተው ፓርላማ ለመቀመጥ የተስማሙትንም ሳይቀር ያስደነገጠ ሆኗል። እናም ይህ ውጤት በተስፋ ቋጣሪውም ሆነ በተቀጣሪው ተቃዋሚ አመለካከት ላይ ግዙፍ ለውጥ እንደሚያሥከትል ጥርጥር የለውም።

ይህ የአመለካከት ለውጥ ደግሞ ወደ አንድና ብቸኛ የመፍትሄ ሃሳብ ፍለጋ እንዲያመሩ ግድ ማለቱም አይቀርም፡፡ ሁሉም ትናት የተጓዙበት ጎዳና እንዳላዋጣቸው አውቀዋል። ጥያቄው፡- ወደፊትም በዚሁ ጎዳና መጓዝ እንደማያዋጣቸውስ ሁሉም አውቀዋልን? የሚል ይመስለኛል። ለዚህ ጥያቄ የምናገኘው ምላሽ የቀጣዩ የትግል ጉዞ መሰረት ነው። የኃይል አሰላለፉን የሚወስን።

እንግዲህ ከምርጫው ውጤት የወያኔን ወደ ፍጹም አምባገነን መንግስትነት መለወጥ ከተረዳን፤ መፍትሄ ብለን የምንቀይሰውም ዘዴ አምባገነን መንግስታትን ለመቋቋም የሚያስችል ሊሆን ግድ ይላል። ኃይልን ያማከል የትግል ስልት..! አስገዳጅነትን ያካተተ የትግል እንቅስቃሴ...! ይህው ነው!

ቸር ይግጠመን

አ.ጌ

azebgeta@gmail.com